# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 313 ግንቦት 1 2006 ገጽ


ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!!! አውቀውም ሆነ ሳያውቁ በወያኔ ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ ተጠልፈው ንግግራቸው ሰው ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የሚያቃቅሩ ሰዎችን አትስማ። የመረረ፣ የሚያስቆጣ ንግግር እንኳን ቢናገሩ ንቀህ ተዋቸው። በወያኔ ውስጥም ሆነ ከወያኔ ውጭ ሆነው ብሔርና ዘርን እያነሱ ተማረው ማስመረር የሚሹ ሁሉ ግባቸው አንድ ነው። በየትናቸው ወገን ቢሆኑ እነሱ የጥፋት ኃይሎች ናቸው፤ እነሱ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጠላት የሆነው የህወሓት መጠቀሚያ ናቸው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከአሜሪካና አውሮፓውያን ጋር የነበረው ግንኙነት መሻከሩ ታወቀ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከአሜሪካና አውሮፓውያን ጋር የመሰረተው ግንኙነት ከቶውንም ንፋስ እንደማይገባው የወያኔ ቱባ ካድሬዎች ሲደሰኩሩ መስማት የተለመደ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ፋሽስቱ ህወሃት ከነዚሁ የአለም ሃያላን አገራት ጋር አስሮት የነበረው ቀለበት መወየቡ በስፋት እየተነገረ መሆኑ ታውቋል። በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አሜሪካ ለፋሽሲቱ ህወሃት የምትሰጠውን ጭፍን ድጋፍ ያዝ ማድረጓና፤ ፋሽስቱ ወያኔ ከአሜሪካ እርዳታ ለማግኘት የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት እንደሚጠበቅበት የሚያትት ህግ ረቆ መፅደቁ የህወሓት ቱባ ካድሬዎች በአገርና ህዝብ ስም የሚያደርጉትን ዘረፋ ማሽመድመዱን ተከትሎ በህወሓት መንደር ቁጣ መቀስቀሱ የሚታወስ ነው። በአሜሪካን ኮንግረስ የፀደቀው አዲስ የውሳኔ ሕግ አሜሪካ ለጉጅሌው ወያኔ የምትሰጠው ርዳታ በትክክል ህዝብን ሳይጎዳ በስራ ላይ መዋሉንና አለመዋሉን እንዲቆጣጠር ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መ/ቤት (State Department) ትዕዛዝ የተላለፈበት እንደነበር ይታወሳል።

አምባገነኑ ወያኔ በሐገርና በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው አፈና፤ ግድያ፤ የዜጎች መፈናቀል ባጠቃላይ በአገዛዙ የሚፈፀሙ መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፤ ብሎም አገዛዙ በዲሞክራሲ ስም የሚያደርገው ቁማር ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የአዲስ አበባ ህዝብ ከአንድነት ፓርቲ ጋር በመሆን እሪታውን አሰማ!

ባለፈው እሁድ የአንድነት ፓርቲ የእሪታ ቀን በሚል የጠራው የተቃውሞ ሰልፍ በተሳካ ሁኔታ መደረጉን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በከተማዋ ያሰፈነውን ሙስናና ያላግባብ በስልጣን መባለግ፤ የመብራት ውሃ እና ኔትወርክ ችግር፤ የፖለቲካ መሪዎች ጋዜጠኞች እና ጦማርያን እስር፤ የሃይማኖት መሪዎችና ፍትህ የጠየቁ ዜጎች ወደ ወህኒ መወርወርና የአገዛዙ ቅጥ ያጣ የእምነት ጣልቃ ግብነት ወዘተ የመሳሰሉት የህዝብ ብስቶችን እና ጥያቄዎችን በመያዝ በአስር ሺዎች የሚቆጠር የአዲስ አበባና አካባቢዋ ነዋሪ አድባባይ በመውጣት ድምጹን ማሰማቱ ታውቋል።

በህዝባዊ የተቃውሞ ሰልፉ ላይ የተለያዩ የህዝብ ብሶቶችን ያስተጋቡ መፈክሮች የተሰሙ ሲሆን ህዝቡ ውሸት ሰለቸን!!! መብትን መጠየቅ ሽብር አይደለም!! ወኔ የሌለው ህዝብ የአገር ሸክም ነው!! ፍትህን ያሉ ቃሊቲ ገቡ!! ፍራቻው ይቅር ተቀላቀሉ!! ድል የህዝብ ነው!! ድምጻችን ይሰማ!! በማለት ህዝቡ በአገዛዙ ላይ የእሪታ ድምጹን አሰምቷል። በፋሽስቱ ወያኔ መታሰር ይብቃ! ጭቆናው ይብቃ! መሰደድና መገደል ይብቃ! ዞን ዘጠኝ ጦማርያን ባስቸኳይ ይፈቱ! ኮሚቴው ይፈታ <<በአገራችን ሰላም አጣን >> በማለት ሰልፈኞቹ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ምሬትና ብሶት አስተጋብተዋል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ለፋሽስቱ ወያኔ ቁንጮ ሟቹ መለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ግንባታ በሚል ህዝቡ ገንዘብ እንዲያዋጣ እየተገደደ መሆኑ ተሰማ

የፋሽስቱ ህወሓት ቁንጮ ለነበረውና በግፍ ኢትዮጵያውያንን በማስጨፍጨፍ፤ በማሰርና በማሰደድ ብሎም ለአገሪቱ የማይበጅ የጎሳ ፖለቲካን በመዘርጋት የክፋት መርዙን በመርጨትና ህዝብን ከህዝብ በማፋጀት የአገዛዙን እድሜ ለማርዘም ሲታትር ባጭሩ ለተቀጨው ለሟቹ መለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ለማቋቋም በሚል በጉጅሌው የህወሓት ቡድን እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወሳል። ለነፍሰ በላው መለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ግንባታ በሚል ዘረፋ የጀመረው የፋሽስት ቡድን በቅጥረኛ ካድሬዎች አማካኝነት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ቤት ለቤት እየዞሩ ህዝቡን ለፋውንዴሽን ማቋቋሚያ ብር ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

# ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የጉጅሌው ወያኔ በአባይ ላይ መገንባት የጀመረው ግድብ የህወሓት ድርጅቶችን ትርፍ በእጥፍ ማሳደጉ ተሰማ

የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ህዝብን በማወናበድ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በማሰብ ካለ ዕቅድና ጥናት በአባይ ወንዝ ላይ መገንባት የጀመረው ግድብ የዘራፊውን የህወሓት ድርጅቶች ትርፍ በእጥፍ ማሳደጉን የውስጥ ምንጮቻችን ለሬዲዮ ክፍላችን የላኩት መረጃ ያመለክታል። እንደ የውስጥ ምንጮቻችን መረጃ ለግድቡ ግንባታ ከሚያስፈልጉ ጥሬቃዎች እስከ ተራ ካፍቴሪያና የምግብ ሽያጭ አገልግሎት በዘራፊው የህወሓት ድርጅቶችና ለአገዛዙ ቅርበት ባላቸው ሰዎች መሸፈኑ የታወቀ ሲሆን ከትናንሾቹ የህወሓት ድርጅቶች መካከል አንዱ የሆነውን የህትመት ተቋም ገቢ ለማድለብ በማቀድም የሟቹ መለስ ዜናዊ ምስል ያረፈበት የ100 እና 50 ብር ኩፖኖችን በማተም ለግብይይት አገልግሎት እንዲውሉ መደረጉ ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የግድቡን ግንባታ በበላይነት የሚመሩትና ለቁጥጥር የተመደቡት ግለሰቦችና ወታደሮች ከአንድ የዘር ዘውግ ብቻ የተሰባሰቡ መሆናቸው ያሳዘናቸው በርካታ ጎብኝዎች የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ይህን ለምን ማድረግ እንደፈለገ ቢጠይቁም ማስፈራሪያ የታከለበት ስድብ እንጅ አጥጋቢ ምላሽ እንደማይሰጣቸው ታውቋል። ይህን ተከትሎ በርካታ የውስጥ ሰራተኞች በተለይም ምሁራን ባለሞያዎች በየጊዜው ስራቸውን እየለቀቁ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል። በጉብኝት ወቅት የተሰጡ አስተያየቶች በሚል በወያኔው ቴሌቪዥን የሚቀርቡ የህዝብ አስተያየት ተብየዎችም ለፕሮፖጋንዳቸው ይረዳ ዘንድ የአገዛዙ ቅጥረኞች ጎብኝዎችን በማስገደድ የግድቡ ምስል ያረፈበትን ቲሸርትም እንዲለብሱ በማድረግ እንደሚቀረጹና ለእይታ እንደሚውሉ ማስረጃው ያሳያል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዘራፊው የህወሃት ቡድን ካለ በቂ ዕቅድና ፕላን ተጀምሮ ለህዝቡ ዕዳ የሆነው የአባይ ግድብ በታቀደለት ጊዜ እንደማይጠናቀቅ መረጃው የሚያሳይ ሲሆን ህዝቡ የፋሽስቱ ህወሓት ቡድን በግድቡ ግንባታ ላይ እያደረገ ያለውን ንግድና ዘረፋ ብሎም የፖለቲካ ቁማር እንደ ባለቤትነቱ ሊጠይቅና ሊያስቆም እንደሚገባም በአንክሮ ያሳስባል።

## ወንድሞቻቸዉ የተገደሉባቸዉ የሃሮማያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትምህርት ለመጀመር ድፍረቱ እንደሌላቸው አስታወቁ

ከአረመኔ የአግአዚ አልሞ ተኳሾች ጥይት ለማምለጥ ድሬዳዋና ሃረር ዉስጥ በየአብያተ ክርስቲያናትናቱና በየግለሰቦች ቤት ተሸሽገው የሚገኙ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚታየው የጸጥታ ሁኔታ እጅግ በጣም የሚያስፈራ በመሆኑ በአጭር ግዜ ዉስጥ ወደ ትምህርት ገበታቸዉ እንመለሳለን የሚል እምነት እንደሌላቸዉ ተናገሩ። የወያኔ አገዛዝ እሱ እራሱ ሆን ብሎ የፈጠረዉ መናገትና አለመረጋጋት መርገቡን በመግለጽ ከግቢ የወጡ ተማሪዎች ተመልሰው እንዲገቡና ትምህርት እንዲጀምሩ ጥሪ ቢያቀርብም፣ አንዳንድ ግቢውን ጎብኝተው የተመለሱ ተማሪዎች ግን ሁኔታው አሁንም አስፈሪ በመሆኑ ትምህርት ለመጀመር ፍላጎት የለንም ብለዋል። አንድ ተማሪ ” በተማሪዎች መካከል መተማመን በመጥፋቱ ፣ በውጭ ያሉ ተማሪዎች ዶክመንታቸውንና ልብሶቻቸውን ይዘው ወደ አካባቢያቸው ከመመለስ ውጭ የመማር ፍላጎት የላቸውም” ብሎአል። በሌላ በኩል ደግሞ በኦሮምያ ክልል የህወሃትና የኦህዴድ ካድሬዎች እየነዙት ያለው በአንድ ብሄር ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ዘመቻ ያሰጋቸው አንዳንድ ኢትዮጵያውያን፣ ህዝቡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ እንዲያደርግ እየመከሩ ነው። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ ዞን ዘጠኝ ጦማሪያንና ጋዜጠኞችን በአሸባሪነት ለመክሰስ ጉድጉዱን ጀመረ

ዜጎች ሀሳባቸዉን በንግግርና በጽሁፍ ሲገልጹ አይኑን የሚያመዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በግፍ ሰብስቦ ያሰራቸዉ ጦማሪያንና ጋዜጠኞች ፍርድ ቤት ቀርበው “ፖሊስ መረጃ እስኪሰበስብ ድረስ” በሚል ሰበብ የ10 ቀናት የጊዜ ቀጠሮ የተጠየቀባቸው መሆኑን የፍርድ ቤቱን ሁኔታ በስፍራዉ ተገኝተዉ የተከታተሉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ገለጹ። ወያኔ በግፍ ተነሳስቶ ያሰራቸዉን ጋዜጠኛ ተስፋለም ወልደየስ፣ ጋዜጠኛ አስማማው ሃይለጊዮርጊስ፣ ጸሃፊ ዘላለም ክበረት፣ ናትናኤል ፈለቀ፣ አጥናፍ ብርሃነና ኤዶም ካሳየን አርቲክል 19 እየተባለ ከሚጠራው የውጭ ድርጅት ጋር ግንኙነት ፈጥራችሁ የግንቦት 7ን ፤ የኤርትራንና የግብፅን ተልዕኮ ታስጽማላችሁ በሚል የፈጠራ ክስ ከስሶ ዕድሜ ልካቸዉን እስር ቤት እንዲኖሩ ለማድረግ በመሯሯጥ ላይ መሆኑን ብዙ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ከአዲሰ አበባ የላኩልን ዜና ይጠቁማል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔን ውድቀትና የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማፋጠን ኅብረታችን ይጠንክር!!!

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በግፍ ሕይወታቸው ባጡ ዜጎች መርዶ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እና ቁጭት ይገልፃል፤ ለቤተሰቦቻቸውም መጽናናትን ይመኛል። ህወሓት እና አጋፋሪው አህዴድ በነዙት ሽብር ሳቢያ የአካል ጉዳት የደረሰባችሁ፣ የተደበደባችሁ እና ለእስር የተዳረጋችሁ ወገኖቻችንም ህመማችሁም እስራችሁም የሁላችንም ነው። መላው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ ከእናንተ ጋር ተገድሏል፣ ቆስሏል፣ ተደብድቧል፣ ተግዟል፣ ታስሯል። ህወሓት፣ አህዴድ እና በዚህ ጭፍጨፋ እጃቸው ያለበት ሁሉ ከተጠያቂነት የማያመልጡ መሆኑን ግንቦት 7 ደጋግሞ ያስገነዝባል።

በህወሓት ዘረኛና ፋሽስታዊ አገዛዝ ያልተበደለ የኢትዮጵያ ክፍል የለም። የወያኔ አጋፋሪ የሆነው አህዴድ የኦሮሞ ወጣቶችን፣ ሕፃናትንና አዛውንትን ሲጨፈጭፍና ሲያስጨፈጭፍ፣ ሌላው አጋፋሪ ብአዴን ደግሞ በጎንደርና አካባቢው ተመሳሳይ ጭፍጨፋዎችን አካሂዷል። ወያኔ ከፋሺስት ኢጣልያ ወርሶ ለሃያ ዓመታት በትጋት ያራመደው "የከፋፍለህ ግዛ" ፖሊሲ ምርት እነሆ ዛሬ በዓይኖቻችን እያየን ነው። ፋሽስት ጣልያን ጀምሮት የነበረውን ኢትዮጵያን የማጥፋት ስትራቴጂ ለማጠናቀቅ ህወሓት በጥድፊያ ላይ ነው። ይህን እኩይ ዓላማ ማስቆም የሁላችን ኃላፊነት ነው።

የመከላከያ ሠራዊት እና የፌደራል ፖሊስና አባላት ሆይ፣ ለዘረኛው ወያኔ መሣሪያ ሆናችሁ ወገናችሁን አትፍጁ! እናንተ የምታገለግሉት ሥርዓት፣ ከእናንተ መካከል ኦሮሞ ያልሆኑት እየመረጠ ኦሮሞዎች ወገኖቻችንን እንዲገሉ፣ አማራ ያልሆኑት ተመርጠው አማሮችን እንዲገሉ የሚልክ መሠሪ መሆኑን የምታውቁት ነው። ወኔን አንዳችንን በሌላችችን ላይ እያዘመተ እርስ በርስ ሊያፋጀን ቆርጦ መነሳቱን አስተውሉ። ይህን እኩይ ዓላማ የማክሸፍ ሥራ የናንተም ኃላፊነት እንደሆነ ግንቦት 7 ያስገነዝባል።

በወያኔ የስለላ መዋቅር ውስጥ ያላችሁ ህሊና ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን የምትሠሩት ሥራ አገራችን ወደየት ሊወስዳት እንደሚችል ቆም ብላችሁ አስተውሉ። እናንተ ዛሬ የምትወስዱት ቆራጥ እርምጃ የበርካታ ሕዝብ ሕይወት ሊታደርግ ይችላል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች በተለይም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተከፋፍላችሁው ወያኔን መቃወም የትም አያደርስም። በኦሮሞው መገደል አማራው፣ ትግሬው፣ ወላይታው፣ ጉራጌው ካላመመው፤ አማራው ሲበደል ኦሮሞውና ሌላው እንዲያመው እንዴት መጠበቅ ይቻላል። እናንተ ወጣቶች ከዘውግ ቆጠራ በላይ ሁኑ። ዛሬ የሚደረጉ ትናንሽ ነገሮች እንኳን የረዥም የወደፊት ውጤት እንዳላቸው ተገንዘቡ። የወደፊቱ ኢትዮጵያ የእናንተ ናት፤ የምትመኟትን ከራሷ ጋር የታረቀች ኢትዮጵያን ለመፍጠር በቅድሚያ እናንተ መታረቅ ይኖርባችኋል። የሁላችንም ቀንደኛ ጠላት ወያኔ ነው ትኩረታችሁን እሱ ላይ አድርጉ።

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!!! አውቀውም ሆነ ሳያውቁ በወያኔ ዘረኛ ፕሮፖጋንዳ ተጠልፈው ንግግራቸው ሰው ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የሚያቃቅሩ ሰዎችን አትስማ፣ የመረረ፣ የሚያስቆጣ ንግግር እንኳን ቢናገሩ ንቀህ ተዋቸው። በወያኔ ውስጥም ሆነ ከወያኔ ውጭ ሆነው ብሔርና ዘርን እያነሱ ተማረው ማስመረር የሚሹ ሁሉ ግባቸው አንድ ነው። በየትናቸው ወገን ቢሆኑ እነሱ የጥፋት ኃይሎች ናቸው፤ እነሱ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጠላት የሆነው የህወሓት መጠቀሚያ ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ህወሓት እና ህወሓት የዘረጋው ሥርዓት ነው። የጋራ ትኩረታችን በጋራ ጠላታችን ላይ ብቻ ይሁን። ወያኔ ትኩረታችንን ለመበተን ብዙ ነገሮችን ይጀምር ይሆናል፤ ርስ በራሳችን ከማባላትም አልፎ ጎረቤቶቻችንን መጎነታተል ይጀምር ይሆናል። በእንዲህ ዓይነት ድርጊት ትኩረታችን መበተን ፈጽሞ የለበት።

እኛ ኅብረታችንን ስናጠናክር የተዳከመው ወያኔ ይበልጥ ይዳከማል። ሊበታትኑን የዳከሩትን አሳፍረን ኅብረታችን እናጠነክራለን። ይህ ደግሞ የወያኔ ውድቀት እና የኢትዮጵያ ትንሣኤን ያፋጥናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከአሜሪካና አውሮፓውያን ጋር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አሜሪካንና የፋሽሱቱ ህወሓት ግንኙነት እንዳሻከረውና ይህን ተከትሎ የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ፊቱን ወደ ቻይና እንዲያዞር አድርጎታል ሲሉ በርካቶች አስተያየታቸውን እየሰጡ ይገኛሉ። ፋሽስቱ ወያኔ በአሁኑ ሰአት ለስራ ጉብኝነት ኢትዮጵያ ለሚገኙት የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ጆን ኬሪ የተደረገው ቀዝቃዛ አቀባበል የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ከአሜሪካ ጋር የነበረው ወዳጅነት ማከተሙን ያመላከታል ሲሉ አስተያየታቸውን ያጠናክራሉ። የፕሬስ ነጻነት፣ የመናገርና የመሰብሰብ ነጻነት፣ የህግ የበላይነት፤ ወዘተ ህወሓት እንዳሻው በሚያሾራት ኢትዮጵያ በአገዛዙ መጣሳቸው የአሜሪካን ብሎም የአውሮፓውያን ባለስልጣናት ከፋሽስቱ ህወሓት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በአንክሮ እንዲያጤኑ እንዳስገደዳቸውም ለማወቅ ተችሏል።

ጉጅሌው ህወሓት ከእነዚሁ ሃያላን አገሮች ጋር የነበረው ግንኙነት ወደ መቃቃር ደረጃ መድረሱን በቅርቡ የወያኔው ቴሌቪዥን ጣብያ የቀለም አብዮት በሚል ርዕስ ባቀረበውን የዶክመንታሪ ድራማ ማወጁ የሚታወስ ነው። እንደሚታወቀው በሙስና የነቀዘው የህወሓት አገዛዝ ከጠቅላላ የምዕራባውያን መንግስታት ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕርዳታ በየዓመቱ ያገኝ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን ይህ ከፍተኛ መጠን ያለው ዕርዳታ ከአጠቃላይ አመታዊ በጀቱ 50% የሚሆነውን ይሸፍንበት እንደነበር ይነገራል። ፋሽስቱ ህወሓት ከአሜሪካን ብቻ አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ዶላር በየዓመቱ በዕርዳታ መልክ ያገኛል የነበረ ሲሆን ይህም ርዳታ ብቻውን የበጀቱን አንድ ሶስተኛውን ይሸፍን እንደነበር ይታወቃል።

## ለፋሽስቱ ወያኔ ቁንጮ ሟቹ መለስ ዜናዊ ፋውንዴሽን ግንባታ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እንዲከፍሉ እያስገደዱት መሆኑን ከምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በመላ አገሪቱ ከከተማ እስከ ገጠር ገበሬዎች፣ የመንግስት ሰራተኞች፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለፋውንዴሽኑ በግዳጅ ገንዘብ እንዲያዋጡ መደረጋቸው በርካታ ነዋሪዎችን ማስቆጣቱ የታወቀ ሲሆን የመንግስት ሰራተኞችም ካለፍላጎታቸው ከፋይናንስና ከሲቪል ሰርቪሱ ሕግ በተቃራኒ ከደሞዛቸው እንዲቆረጥባቸው በዘራፊው የህወሓት ቡድን ትዕዛዝ መተላለፉም ታውቋል።

በዚህ መመሪያ የተበሳጩ የመንግስት ሰራተኞች "ወዴት እንሂድ" በማለት ምሬታቸውን እየገለጹ ሲሆን ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ግለሰቦች እንዳሉት በቁሞ አራቁቶንና መቀመቅ ውስጥ ከተቶን ለሞት ነፍስ በላ መሪ ቤሳ ቤስቲን ማዋጣት አንፈልግም ሲሉ ቁጣ የተቀላቀለ አስተያየታቸውን እየሰጡ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል። እያንዳንዱ ህዝብ ገንዘብ እንዲያወጣ መገደዱ አግባብ አለመሆኑን የተናገሩት አስተያየት ሰጭዎች ገንዘብ መስጠትም ካለባቸውም በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ እየተጠቀሙ ያሉ ቡችላ ካድሬዎች እንጂ ምስኪኑና በአገዛዙ እየተረገጠና እየተሰቃየ የሚገኘው ጭቁን ህዝብ መሆን የለበትም ሲሉ ምሬት የተቀላቀለበት አስተያየት እየሰነዘሩ ይገኛሉ።

በተያያዘ ዜና በአዲስ አበባ የቀበሌ እድሮች በነፍስ ወከፍ ከ8 ሺ ብር ጀምሮ እንዲከፍሉ የሚያስገድድ መመሪያ ከዘራፊው የህወሓት ቡድን የተላለፈላቸው መሆኑ የታወቀ ሲሆን ይህን ተከትሎም የግዳጅ መዋጮው በበርካታ የእድር አባላት ላይ ከፍተኛ ቅሬታ መፍጠሩ ታውቋል።

ፋውንዴሽኑ የሙስና ንግስት በመባል በምትታወቀው በሚቺ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ሊቀመንበርነት የሚመራ ሲሆን ምስረታውም ህዝብን በመዝረፍና በመበዝበዝ የአገዛዙን ካዝና ለማድለብ ታቅዶ የተቋቋመ አንዱ የህወሓት የዘርፊያ ተቋም ነው ሲሉ የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የውስጥ ምንጮች ተናግረዋል።

## ልማታዊዉን መንግስት መታግልም መቃወምም አይቻልም!!!

እራሳቸዉን ‘ደርግ’ በሚል ስያሜ ሰይመዉና “ያለ ምንም ደም እንከኗ ይዉደም” ብለዉ አስከፊዉን የፊዉዳል ስርዐት አሽቀንጥረዉ የጣሉት ወታደራዊ መኮንኖች ለታሪካዊዉ የመሬት ለአራሹ ጥያቄ የማያዳግም መልስ ሰጥተናል እስካሉበት ግዜ ድረስ የብዙ ኢትዮጵያዉያንን ድጋፍ ማግኘት ችለዉ ነበር። እየዋለ ሲያድር ግን በፋሺስት ባህሪያቸዉና በጎታች የፖለቲካና የኤኮኖሚ ፖሊሲያቸዉ የተነሳ ህዝብ አንቅሮ ስለተፋቸዉ ከሚደግፉቸዉ ይልቅ የሚታገላቸዉ በዝቶ “ያለ ምንም ደም” ብለዉ የተነሱት የደርግ መኮንኖች አገሪቱን ለ17 አመታት የደም ገንዳ አደረጓት።

ትግራይን ነጻ እናወጣለን ብለዉ ደደቢት በረሃ የገቡት የዛሬዎቹ ባለሳምንቶች ደግሞ ለትግል ያነሳሳቸዉ አላማም ሆነ ለኢትዮጵያ ያላቸዉ ራዕይ ለህዝብና ለአገር የማይበጅ በመሆኑ አብረዋቸዉ ታግለዉ አዲስ አበባ የገቡትን ድርጅቶች ጨምሮ አብዛኛዉ የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅሮ የተፋቸዉና ጀርባዉን ያዞረባቸዉ ገና ከጥዋቱ ነበር። ሆኖም አንድም የሚቃወማቸዉ ኃይል የጋራ ትግል መጀመር ባለመቻሉ በሌላ በኩል ደግሞ የምዕራባዉያን መንግስታት ከፍተኛ የገንዘብና የድፕሎማሲ ድጋፉ ስላልተለያቸዉ ወያኔዎች ያንን ያክል ህዝብ እየተቃወማቸዉ ዛሬም ተዳላድለዉ ስልጣን ላይ እንደተቀመጡ ነዉ። ከጨቋኙ የፊዉዳል ስርዐት ለመላቀቅ ከአመታት በፊት ትግል የጀመረዉና ትናንት ወታደራዊ አምባገነኖችን የታገለዉ የፈረደበት የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ ደግሞ ዘረኛ አምባገነኖችን እየታገለ ነዉ።

ወያኔ ጫካ ዉስጥ ጀምሮት አዲስ አበባ ዉስጥ ያጸደቀዉ የኢትዮጵያ ህገመንግስት ማንም ሰዉ በዉጭ አገርም ሆነ በአገር ዉስጥ ያለምንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለዉ ይላል፤ ሆኖም ኢትዮጵያ ዉስጥ ይህንን ህገመንግስታዊ መብት ተጠቅመዉ ሀሳባቸዉን በነጻነት ለመግለጽ የሚሞከሩ ዜጎች ዕጣቸዉ ሞት፤ መሰደድና ቃሊቲ መዉረድ ነዉ። የሚገርመዉ የወያኔ ህግ በማይሰራባቸዉ በዉጭ አገሮችም የወያኔን ክፋትና ግፍ አስመልክቶ ሀሳባቸዉን የገለጹ ንጹህ ኢትዮጵያዉያን የሞትና የዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶቸባቸዋል። ሌላዉ የተጻፈበትን ወረቀት ያክል ክብደት የሌለዉ የወያኔ ህገመንግስት ከፈቀዳቸዉ መብቶች አንዱ - ማንም ሰዉ ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነት አለዉ የሚለዉ ህግ ነዉ። ዛሬ በተግባር እንደምንመለከተዉ ወያኔ ሰላማዊ ሰልፍ ያደረጉ ዜጎችን ብቻ ሳይሆን ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አስበዋል ያላቸዉን ሁሉ በሌሊት ከመኖሪያ ቤታቸዉ እየጎተተ ወስዶ ያስራል። ለምሳሌ ህገመንግስታዊ መብታቸዉን ተጠቅመዉ ለእሁድ ሚያዝያ 19 ቀን ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በዝግጅት ላይ የነበሩትን የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎችና አባላት የወያኔ ፖሊስ ከሐሙስ ሚያዝያ 17 ቀን ጀምሮ ከየመኖሪያ ቤታቸዉ ሰብስቦ አስሯል። የወያኔ ዘረኞች እስክንድር ነጋን ለምን ጻፍክ ብለዉ 18 አመት አንዱ አለም አራጌን ደግሞ ለምን ተናገርክ ብለዉ የዕድሜ ልክ እስራት ፈርደዉበታል። በቀለ ገርባንና ኦብላና ሌሊሳን የኦሮሞ ተወላጆች ስለሆኑ ብቻ በጅምላ የኦነግ አባላት ናችሁ የሚል የግፍ ክስ መስርተዉባቸዉ አስር ቤት ዉስጥ እያንገለቷቸዉ ነዉ። በአጠቃላይ የወያኔ መሪዎች እየነገሩን ያለዉ የመናገር፤ የመሰብሰብም ሆነ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት የሚፈቅድላችሁ ህገ መንግስቱ ሳይሆን እኛ ነን፤ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ህግ ማለት እኛ ነን እያሉን ነዉ። ይህ ደግሞ በአፋቸዉ ብቻ የሚናገሩት ሳይሆን ለአመታት በተግባር ያሳዩን ማንም አሌ የማይለዉ ሀቅ ነዉ።

አፈሩን እንደ ጨርቅ ያቅልልለትና - ያ ላይመለስ የተሰናበተን የወያኔ ቁንጮ አንድ ሰሞን እንደኛ ተዋግታችሁ ስልጣን መያዝ ከፈለጋችሁ “መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ” ብሎ መርቆን ነበር። አዎ ይህንን ስድብና ሽሙጥ የሚቀናዉ ሰዉ በሚገባ ያላወቀ ሰዉ በእርግጥም ሰዉየዉ የመረቀን ሊመስለዉ ይችላል። የወያኔዉ ቁንጮ በወቅቱ ማስተላለፍ የፈለገዉ መልዕክት ግን ከእኛ ዉጭ የመሳሪያ ትግል ለአሳር ነዉና አትሞክሩት የሚል ነዉ፤ ወይም ጠቅለል ባለ መልኩ መልዕክቱ ሐሞት የላቸዉምና አያደርጉትም፤ ቢያደርጉትም ችሎታዉ የላቸዉምና ወይ ጀምረዉ ይተዉታል አለዚያም እኛ እናስቆማቸዋለን የሚል ንቀትና ትዕቢት የተሞላበት መልዕክት ነዉ።

የወያኔ ዘረኞች ኢትዮጵያ ዉስጥ የመሪነቱ ቦታ የእኛ ብቻ ነዉ፤ የእናንተ ተግባር አርፋችሁ መገዛት ነዉ ብለዉ ከነገሩን ቆይቷል። ይህ ደግሞ አንዴ ተናግረዉ የረሱት ነገር ሳይሆን በየግዜዉ እየደጋገሙ የሚነግሩን ዋናዉ መልዕክታቸዉ ነዉ። በምርጫ ሞክሩን አሉና የመጫወቻ ሜዳዉን ትንሽ ለቀቅ አደረጉት፤ ግን ህዝቡ ይጠቅመኛል ብሎ ያሰኘዉን ሰዉ ሲመርጥ ድምጹንም ህይወቱንም ቀሙት። ሲገድሉን ፈርተን የምናቅፋቸዉ፤ሲገፉን ዝም ብለን የምናያቸዉ መስሏቸዉ “መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ” አሉን። በህይወታችን ቆርጠን ዱር ስንገባ ሽብርተኞች አሉንና ስማችንን ያነሳዉን ሁሉ እያሰሩ መደብደብና መግደል ጀመሩ።ቀድሞዉንም ቢሆን ወያኔ ምርጫ ምርጫ እያለ የሚያላዝነዉ አንድም ለምዕራባዉያን ለጋሾቹ ፍጆታ እንዲሆነዉ አለዚያም ተቃዋሚዎች ምርጫዉን እንዲያደምቁለት ነዉ እንጂ የፖለቲካ ፓርቲዎች መመረጥ በሚችሉበት መንገድ እንዲወዳደሩት በፍጹም አይፈቅድም። ወያኔ ህገ መንግስቱን አክብራችሁ በሰላማዊ መንገድ መታገል ትችላላችሁ ብሎ ሲነግረን መቼም ለመብትና ለነጻነት የማይሞከር ነገር የለምና ህገመንግስቱን አክብረን በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ህዝቡ መኸል ገብትን ቅስቀሳ ማድረግ ጀመርን፤ የእኛንና የህዝቡን መገናኘት እንደ ጦር የሚፈራዉ ወያኔ ከህዝብ ጋር ለመገናኘት በሞከርን ቁጥር እኛንም መኪናችንንም እያሰረ መደብደብ ጀመረ። የወያኔ ህገመንግስት በግልጽ ካስቀመጣቸዉ መብቶች አንዱ ማንም ሰዉ መሰብሰብና በሰላማዊ መንገድ ተቃዉሞዉን መግለጽ ይችላል የሚል ነዉ፤ ሆኖም ተቃዋሚዎች ሰለማዊ ሰልፍ ልናደርግ ነዉ ብለዉ ሲያሳዉቁት ወያኔ አንዴ ጨርቄን አንዴ ማቄን እያለ ህገ መንግስቱ ለህዝብ ያጎናጸፈዉን መብት ከወያኔ ኪስ ተመዝዞ የሚወጣ ምፅዋት አስመሰለዉ። የወያኔን አይጥነት በሚገባ የተረዱት የሰማያዊ ፓርቲ መሪዎች በነጋ በጠባ ሰላማዊ ሰልፍ ካልተሰለፍን እያሉ ከወያኔ ጋር እይጥና ድመት መሆን ሲጀምሩ የሰልፉን ቦታና ቀን የሚመርጠዉ ሰላማዊ ፓርቲ ሳይሆን ወያኔ እራሱ ሆነ። ባጠቃላይ ዬት፤እንዴትና መቼ አንደምንቃወመዉ የሚመርጠዉ ወያኔ እራሱ ሆኖ አረፈዉ።

የማንሞክረዉ መስሎት “መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ” ብሎ ያሾፈዉ ወያኔ ጀግኖች በሚገባህና በምታዉቀዉ ቋንቋ እናናግርሀለን ብለዉ ጫካ ሲገቡ እነሱን፤ ቤተሰቦቻቸዉንና ስማቸዉን ያነሳዉን ሁሉ እየሰበሰበ ሽብርተኛ ናችሁ ብሎ ማሰር ጀመረ። ባለፈዉ ሳምንት ረቡዕና ሐሙስ ደግሞ ወያኔ ከ23 አመታት የከተማ ቆይታ በኋላ ያ የለመደዉ ህገ አራዊትና የጫካ ዉስጥ ኑሮዉ ትዝ ብሎት አምቦ ዉስጥ ልብስ ለብሶ መንገድ ላይ የሚሄደዉን በሙሉ በጥይት ማጨድ ጀመረ። በተለምዶ “125” በመባል የምትታወቀዉ ዉቧ የአምቦ ከተማ የህጻን፤ የአዋቂና የአዛዉንት እሬሳ እንደ ቆሻሻ ዕቃ በየመንገዱና በየጢሻዉ ተለቀመባት። **እናቶች ልጄን እያሉ ምርር ብለዉ አለቀሱ፤ ህፃናት ተንጫጩ፤ አባቶች ኡኡ አሉ።** ለወትሮዉ ለድፍን ኢትዮጵያ አምቦ ዉኃ የምታንቆረቁረዉ አምቦ ረቡዕ፤ ሐሙስና ዐርብ አግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረዉ የሰዉ ልጅ ደም እንደ ዉኃ ተንቆረቆረባት። አምቦ እንደጥንታዊቷ ቤተልሄም በግፍ ለተገደሉት ልጆቿ አነባች። የዛሬዎቹ ሄሮዲሶችም ልክ እንደ ጥንቱ ሄሮዲስ ህልማቸዉ አዲሱን ትዉልድ ማጥፋት ነዉና ግድያቸዉን በአምቦ፤ በግንደበረትና የኦሮሞ ዩኒቨርሲቲዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ቀጠሉ።

ወያኔ እኛ እስካላስወገድነዉ ድረስ መግደል ጥርሱን ነቅሎ ያደገበት ስራዉ ነዉና ወያኔ ሰዉ ገደለ ሲባል ብዙም አይገርመንም፤ ይልቅ ከወያኔ ስራዎች ሁሉ እጅግ የሚገርመዉ በየከተማዉ ሰላማዊ ሰልፈኞችን በጥይት ከጨፈጨፈ በኋላ በሚያወጣቸዉ መግለጫዎች ግድያዉን ከባንክ ዘረፋ ጋር ማያያዙ ነዉ። በ2005 ዓም የዘረፋችሁትን የህዝብ ድምጽ መልሱ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጣዉ ህዝብ ዉስጥ ከ200 በላይ በመትረየስ ጨፍጭፎ ባንክ ሲዘርፉ ነዉ የገደልኳቸዉ አለ። “የለመደች ጦጣ ሁልግዜ ሽምጠጣ” እንዲሉ ባለፈዉ ሳምንትም የኦሮሞን ህዝብ መሬት እየቀማችሁ የእናንተን ሰው ማበልጸግ አትችሉም ብሎ ሳላማዊ ሰልፍ ከወጡት የኦሮሞ ተማሪዎች ዉስጥ ከ50 ሰዉ በላይ ጨፍጭፈዉ አሁንም እንደለመዱት ባንክ ሲዘርፉ ነዉ የገደልናቸዉ ነዉ አሉ። መቼም ህዝብ መንግሰትን አስፈቅዶ ባንክ ለመዝረፍ ሰላማዊ ሰልፍ የሚወጣዉ በወያኔዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ መሆን አለባት።

ወያኔን በምርጫ እንዳናወርደዉ አስመራጩ፤ ተመራጩና ድምጽ ቆጣሪዉ ወያኔ እራሱ ሰልሆነ ምርጫ በረደረገ ቁጥር የሚያሸንፈዉም ወያኔ ብቻ ሆነ። ህገ መንግስቱ ሰላማዊ ሰልፍ ይፈቅዳል ብለን በሰላማዊ ሰልፍ ተቃዉሟችንን ስንግልጽ የወያኔ አግአዚ ነፍሰ ገዳዮች ኢላማ መለማመጃ አደረጉን፡ ሰንጽፍ ሽብርተኛ ስንናገር ጸረ ልማት ብለዉ አወገዙን። በቅርቡ በተገባደዉ የሚያዝያ ወር መጀመሪያ አካባቢ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ልትበታተን የነበረቻዉን ኢትዮጵያን ከአደጋ ያዳንናት እኛ ነን፤ እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ ትበታተናለች እያሉ ለአመታት ሲዘፍኑ የከረሙትን የሞኝ ዘፈን በቪድዮ አቀነባብረዉ “የቀለም አብዮት ሰለባዎች” በሚል ስያሜ ለህዝብ አቀረቡ። በዚህ ለዘቢስ ድራማ ዉስጥ የወያኔ ዘረኞች የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ የቀለም አብዮት አካሄዳለሁ ብትል ዕጣ ፈለግህ እንደ ዩክሬን መከፋፈል ነዉና ወዮልህ ብለዉ ህዝብን አስጠነቀቁ። እንገዲህ በወያኔ እየተላለፈልን ያለዉ መልዕክት - ምርጫ ማጀብ ነዉ እንጂ ብታሸንፉም አታሸንፉምና አትልፉ፤ ሰላማዊ ሰልፍ ትርፉ ሞት ነዉ፤ የቀለም አብዮት ደግሞ አገር ይከፋፍላል የሚል ነዉ። ባጠቃላይ የወያኔ ዘረኞች ልማታዊ መንግስት ነንና እኛን በምንም መልኩ መቃወም ፀረ አገርና ፀረ ልማት መሆን ነዉ እያሉ ምንም ሳይፍሩ አፋቸዉን ሞልተዉ እየነገሩን ነዉ። ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተቃዋሚ ፓርቲዎቸ ትልቁ ችግር ከህዝባዊ አመጽና ከሰላማዊ ትግል አንዱን መርጠዉ መታገል መቻልና አለመቻል ሳይሆን ወያኔ ልማታዊ መንግስት ነዉና መታገል ቀርቶ መቃወምም አትችሉም መባሉ ነዉ።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ቀለል ባለ አማርኛ ወያኔ መግቢያ እንጂ መዉጪያ የሌለዉ ትልቅ ቤት ዉስጥ ከትቶንና መፈናቸኛ አሳጥቶን ሁላችንንም የግዜና የሂሊና እስረኞች አድርጎናል። እንዳንዉጣ ቤቱ መግቢያ እንጂ መዉጪያ የለዉም፤ አርፈን እንዳንቀመጥ ቤቱ የሚለበልብ እሳት አለበት። ወያኔ ፈቀደም አልፈቀደ ከዚህ ተገፍተን ከገባንበት ረመጥ ዉስጥ እንደ ጭስ ቀዳዳ ፈልገን መዉጣትና ነፃ ሰዉ ሆኖ መመላለስ ከአሁን በኋላ የእኛ ጉዳይ ነዉ እንጂ ከወያኔ የሚመጣልን በጎነት አይደለም። ወያኔን ሃያ ሶስት አመት ሙሉ አይተነዋል ከአሁን በኋላ ከሰሞኑ አምቦ ላይ እንዳሳየን ጭካኔዉና አዉሬነቱ እየባሰበት ይሄዳል እንጂ የሌለበትን መልካም ነገር አያሳየንም። ሰለዚህ ሁላችንም እንደ አንድ ሰዉ ቆመን በህዝባዊ አመጽ ወይም በህዝባዊ እምቢተኝነት ወያኔን ለማስወገድ እንነሳ!

## አፍቃሬ ህወሃት አህዴዶችና ሌሎቹ የኢህዴድ አባላት የቃላት ጦርነት ጀመሩ

በቅርቡ የወያኔ አገዛዝ አምቦ ዉስጥ የጨፈጨፋቸዉን ሰላማዊ የኦሮሞ ታሪዎች በተመለከተ የወያኔ ተለጣፊ በሆነዉ ኦህዴድ ዉስጥ የህወሃት ደጋፊዎች በሆኑና በሌሎች የኦህዴድ አባላት መካከል ከፈተኛ ጭቅጭቅ መፈጠሩን ከወደ አዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች አስረዱ። መሬታችንን አትንኩ፤ የልማት መሬት የሚያስፈልግ ከሆነም ህዝብ የማያካትት ልማት የለምና የኦሮሞ ህዝብ በተለይ ተፈናቃዩ ገበሬ ሳይጠየቅ የሚደረገዉን የመሬት መንጠቅ ሂድት እንቃወማለን ብለዉ የተሰለፉ ተማሪዎች በወያኔ አግአዚዎች ከተገደሉ በኋላ ኦህዴድ ለሁለት ይከፈላል የሚል ከፍተኛ ስጋት በወያኔዎች መንደር እንዳለ ምንጮቻችን ጨምረዉ ተናግረዋል።ከአዲስ አበባና የዙሪያዋ ኦሮሚያ የተቀናጀ የጋራ ልማት መሪ ፕላን ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ሰሞኑን ከስድስት በላይ በሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች በተቀጣጠለው ተቃውሞ ምክንያት የኦሮሞ ተማሪዎች በአጋዚ ልዩ ኃይልና በፌዴራል ፖሊስ አባላት መገደላቸው ኦህዴድን ለሁለት ሊከፍል የሚችል ክስተት ሆኖ ብቅ ማለቱን ምንጮች ገልጸዋል።

በኦህዴድ ድክመት ምክንያት ስለማስተር ፕላኑ አስቀድሞ ሕዝቡ ተወያይቶበት ውሳኔ ሳይሰጥበት ወደ ትግበራ መገባቱ የመጀሪያውና ትልቁ ስህተት ነው ያሉት ምንጮቻችን ፕላኑ ወደ ትግበራ ሲተላለፍ በርካታ የኦህዴድ አባላትና አንዳንድ ከፍተኛ ካድሬዎች ጭምር ደስተኛ እንዳልነበሩ ጠቅሰዋል።
በብዙዎቹ የኦህአዴድ አባላትና ካድሬዎች ዘንድ ኦሮሚያ ከአዲስአበባ ማግኘት ያለባት ጥቅም ሳይረጋገጥ እንደገና በአዲስአበባ ዙሪያ ያሉ ከተሞችን ወደ አዲስአበባ ለማካለል የማሰቡ ጉዳይ እንዳልተዋጠላቸውና በዚህም ምክንያት በየመድረኩ ቅሬታቸውን ሲገልጹ መቆየታቸውን፣ በአንጻሩ የኦህዴድ ከፍተኛ አመራሩ ይህንን ቅሬታ በመከላከል ሲያዳፍንና ቅሬታ አቅራቢዎችን በአነግነትና በጠባብነት እየፈረጀ ሲያሸማቅቅ መኖሩን ያስታወሱት ምንጫችን፣ በዚህ ምክንያት በኦህዴድ ውስጥ በሚታይ መልኩ ከአዲስአበባ ጋር ተያይዞ የኦሮሚያ ጥቅም መጠበቅና መረጋገጥ አለበት በሚል እና ይህን ጥያቄ በሚቃወሙ የህወሃት ደጋፊ የኦህዴድ አመራሮች መካከል ግልጽ ሽኩቻ እየታየ መሆኑ ድርጅቱን ለሁለት ሊሰነጥቀው ይችላል የሚል ስጋት አሳድሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኦህአዴድ ከፍተኛ አመራሮች ለችግሩ መንስኤ የኦነግ አባላትና የውጪ ኃይሎች ናቸው በሚል ውጫዊ ምክንያት እየደረደሩ መሆኑ ውስጣዊ ችግራቸውን ለመሸፋፈን ሆን ብለው ያደረጉት ነው ያሉት ምንጫችን፣ የውስጥ ሽኩቻቸው አድጎ የደሃውን ገበሬ ልጆች ሕይወት መቅጠፉ እጅግ አሳዝኝ እንደሚያደርገውም ጠቁመዋል፡፡ ሰሞኑን ከስድስት በላይ በሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ማለትም በአምቦ፣ በነቀምት፣ በሐረማያ፣ በአዳማ፣ በድሬዳዋ፣ በመደወላቡ፣ በተቀሰቀሰው አመጽ ወደ70 የሚጠጉ ተማሪዎች መገደላቸውን የተለያዩ ምንጮች ሲገልጹ ፣ መንግስት የሟቾችን ቁጥር ወደ 10 ዝቅ በማድረግ ሰዎች መሞታቸውንና መንስኤውም ጸረ ሰላም ኃይሎች መሆናቸውን መግለጹ ይታወሳል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ዘጠነኛ መሪ ፕላን የአገልግሎት ዘመኑ መጠናቀቁን ተከትሎ ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ አሥረኛውመሪ ፕላን በመዘጋጀት ላይ ሲሆንየመሪ ፕላን ዝግጅቱ የአዲስ አበባን ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ ከተማ ዙሪያየሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞችን ማለትም ሱሉልታ፣ ቡራዩ፣ መናገሻ፣ ለገጣፎ፣ ለገዳዲ፣ ገላን፣ ዱከምና ሰበታበዚሁ እንዲካተቱ ተደርጎ ፕላኑ እየተዘጋጀ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ ለማውገዝ በተለያዩ የአለም ክፍሎች የሚደረገው የተቃውሞ ሰልፍ ቀጥሎአል።

## የአዲስ አበባ ህዝብ ከአንድነት ፓርቲ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በአገሪቱ አራቱ ማዕዘናት እየተቀጣጠለ ያለው ህዝባዊ ተቃውሞና እምቢተኝነት የጉጅሌው ህወሓት ቡድንን ጭንቀት ውስጥ እንደከተተው የታወቀ ሲሆን የአንድነት ፓርቲ ፕሬዚዳንት ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው በሰልፉ ላይ ባሰሙት ንግግር፤ ባለፉት ቀናት በተለያዩ አካባቢዎች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና ትምህርት ቤቶች፤ የተካሄደዉ የግድያ የድብደባ እና የእስራት እርምጃዎችን «ግዙፍ የሠብዓዊ መብት ጥሰቶች» ሲሉ በጥብቅ አዉግዘዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በያዝነዉ ሳምንት መጀመርያ አዲስ አበባን የጎበኙት የአሜሪካን የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጆን ኬሪ ኢትዮጵያ ለሲቪክ ማኅበራትና ለጋዜጠኞች የተሻለ ነፃነት እንድትሰጥ መጠየቃቸዉ እና ባለፈዉ ሳምንት ማለቂያ የታሠሩት የድረ-ገፅ ጸሀፍትና ጋዜጠኞች ጉዳይም እንዳሳሰባቸዉ መግለፃቸዉ ይታወቃል። ጋዜጠኞች በህትመት፤ በኢንተርኔትም ሆነ በትኛዉም ዓይነት መገናኛ ብዙሃን የሚያከናዉኑት ኅብረተሰቡን እንደሚያጠናክር፤ እንደሚያነቃቃና፤ ለዴሞክራሲም መጠናከርና ድምፅ ሲሆን እንደሚችልም ኬሪ መግለፃቸዉ ይታወሳል።

## የወያኔ ካድሬዎች በኦሮሚያ የተነሳውን ግጭት የብሄር ግጭት ለማስመሰል ዘመቻ መጀመራቸው ታወቀ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ከግዜ ወደ ግዜ እያየለ የመጣዉ ህዝባዊ እምቢተኝነት ክፉኛ ያስደነገጠዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ካድሬዎችን ህዝባዊ ጥያቄዎች ወ ተነሱበት አካባቢ ሁሉ በመላክ ከአህዴድ ምንጮች ባገኘው መረጃ ተንተርሶ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በአማራና በኦሮሞ ህዝብ መካከል ልዩነትን በመዝራት ሁለቱን ታላላቅ የኢትዮጵያ ብሄሮች ለማጋጨት በከፍተኛ ደረጃ ዕቅድ አቅደዉ በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸዉ ተጋለጠ። ይህንን እርሰኩስ የወያኔ ሴራ ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የተሰማሩ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች የአማራና ኦሮሞ ወጣቶች እንዲጋጩ ከፍተኛ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሎአል።በሃሮማያ እና በድሬዳዋ ዩኒቨርስቲዎች አንዱን ብሄር የሚያጥላሉ ንግግሮች ሆን ተብሎ ተልእኮ በተሰጣቸው ካድሬዎች እየተነገሩ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም ተመሳሳይ ልዩነት ለመፍጠር እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል።

ካድሬዎቹ በቅርቡ በባህርዳር ከተማ በተካሄደው የስፖርት ፌስቲቫል ላይ አማራ ኦሮሞዎችን ተሳድቧል የሚል ወሬ በመንዛት የኦሮሞዎችን ስሜት ለመቀስቀስ እየሞከሩ መሆኑን ምንጮች ገልጸዋል። ህወሃት ሆን ብሎ ያሰማራቸው ጥቂት ካድሬዎች በባህርዳር ያሰሙትን ዘለፋ ሆን ብሎ የመላው አማራ ህዝብ አቋም አድርጎ በማድረግ ግጭት ለመፍጠር የሚንቀሳቀሰው ህወሃት ፣ የአብዛኛውን ህዝብ ትኩረት ባያገኝም በወጥመዱ ውስጥ የገቡ ጥቂት ተማሪዎች፣ የህወሃትን አጀንዳ እያራገቡ መሆኑን ምንጫችን ገልጿል።

በአገራችን እየታየው ያለው ሁኔታ አስፈሪ መሆኑን እና ህዝቡ ለዘመናት ተቻችሎና ተከባብሮ እንደኖረው ሁሉ አሁንም በካድሬዎች ቅስቀሳ ሳይታለል ጊዜውን በጥንቃቄ ማለፍ እንደሚገባ በርካታ አስተያየት ሰጪዎች በኢሳት ላይ እየገለጹ ነው። ከቀናት በፊት አዳማ ውስጥ ተካሂዶ በነበረው የኦህዴድ ስብሰባ እውቁን የሰብአዊ መብት ተማጋቹን አርቲስት ታማኝ በየነን የሚዘልፉና አማራውን የሚያንቋሽሹ ንግግሮች ሲደረጉ እንደነበር እንዲሁም በኦሮምያ የተነሳውን ተቃውሞ የዘር ጉዳይ አድርጎ ለማቅረብ አመራሮች የማሳመን ስራ ሲሰሩ እንደነበር የኢሳት ታማኝ ምንጮች ገልጸዋል።በሌላ ዜና ደግሞ በሚዳቀኝና ባለሚ አካባቢዎች ትናንት በበርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች፣ እናቶችና ሽማግሌዎች ታፍሰው መታሰራቸውን የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሳት ገልጸዋል። አንድ የአይን እማኝ የፌደራል ፖሊስ አባላት ልጆችን እንደ ሚዳቆ እያባረሩ እየያዙዋቸው ነው ሲሉ ተናግረዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች አምቦ ላይ ከፈጸሙት ወንጀል እራሳቸዉን ነጻ ለማድረግ እየሞከሩ ነዉ

የአዲስ አበባን አዲሱን ማስተር ፕላን በመቃወም በአምቦና አካባቢው በሚገኙ ከተሞች ወደ አደባባይ የወጡትን ከ40 በላይ ንጹሃን ዜጎች አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ያስገደለው መንግስት ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን የጀመረውን ፕሮፓጋንዳ በስፍራው ላይ የነበሩ አንዳንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውመውታል። አፈ ጉባኤ አባ ዱላ ገመዳ በኢቲቪ ቀርበው የተማሪዎችን ጥያቄ አነግ እና ግንቦት7 የተባሉት አሸባሪ ቡድኖች አይዟችሁ በማለት አቀጣጥለውታል ብለው ተናግረዋል።

የተማሪዎቹ ጥያቄ ፍትሃዊ ቢሆንም፣ ሌሎች ሃይሎች ግን መጠቀሚያ አድርገውታል በማለት አፈ ጉባኤው አክለዋል።ጉዳዩን በማስመልከት ጥያቄ ያቀረብንለት የ3ኛ አመት የአምቦ ዩኒቨርስቲ ተማሪ እንደተናገረው አባ ዱላ ገመዳ የተናገሩት ፍጹም ሀሰትና ጨርሶ ያልሆነ ነው ብሎአል።“በመጀመሪያ ጥያቄውን ለማቅረብ ስንሰበሰብ መልስ እንደሚሰጡን ከነገሩን በሁዋላ ወዲያው በፌደራል እንድንከበብ አደረጉ፣ ትንሽ ቆይተው ፌደራሎች አስለቃሽ ጭስ መተኮስ ጀመሩ። በአካባቢው ቆሞ ሲመለከት የነበረው ህዝብ ተማሪዎችን ለምን ትነኩዋቸዋላችሁ ብሎ ከፖሊሶች ጋር መጋጨቱን ተናግሯል።

ሌላ አንዲት ልጃቸው በገፍ የተገደለባቸው እናት በበኩላቸው፣ በብዛት ያለቁት ከ7 አመት እስከ 11 አመት የሆናቸው ምንም የማያውቁ ህጻናት መሆናቸውንና ህጻናቱ ጥይት ለመሸሽ በሚል ወደ ጫካ ሲገቡ ጨካ ውስጥ መገደላቸውን በመግለጽ እነ አባዱላ እርምጃ የተወሰደው ንብረት ስለወደመ ነው የሚለውን አስተያየት አልተቀበሉትም። የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና አለማቀፍ ተቋማት መንግስት በአምቦ እና በተለያዩ የኦሮምያ አካባቢዎች የፈጸመውን ጭፍጨፋ ማውገዛቸው ይታወቃል። ሂውማን ራይትስ ወች ግድያውን የፈጸሙትም ሆነ ትእዛዙን የሰጡት ባለስልጣናት ከተጠያቂነት እንደማያመልጡ መግለጹ ይታወሳል።

## ወያኔ ዞን ዘጠኝ ጦማሪያንና ጋዜጠኞችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የወያኔ አገዛዝ ወጣቶቹ የቀለም አብዮት ለማስነሳት ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶች ገንዘብ እንደተቀበሉ አድርጎ በማቅረብ ፣ በሽብረተኝነት ከተፈረጁት ድርጀቶች ጋር ግንኙነት በመመስረት ወንጀል ሊከሳቸው ማሰቡ ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእስር ላይ የሚገኘውየሙስሊሞችጉዳይመጽሄት አዘጋጅ ጋዜጠኛሰለሞንከበደ ለብይን ተቀጥሮ የነበረ ቢሆንም፣ ዳኛ የለም በሚል ምክንያት ለሰኔ 26 ተቀጥሯል። ጋዜጠኛው ከዚህ ቀደምም ዳኛ የለም በሚል ምክንያት ብይን ሳያገኝ ተመልሷል። በአዳማ ከተማ የተያዙ ሙስሊሞችም እንዲሁ ለአራት ወራት በከፍተኛ ስቃይ በእስር ቤት እንዲያሳልፉ ከተደረገ በሁዋላ ዛሬም ዳኛ የለም በሚል ጉዳያቸው ሳይታይ ወደ ቃሊቲና ቂልንጦ እስር ቤቶች ተመልሰዋል።

## ወንድሞቻቸዉ የተገደሉባቸዉ የሃሮማያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተመሳሳይ ዜናም ሰማያዊ ፓርቲ ”ኢትዮጵያውያን ገዥው ፓርቲ በፈጠረው የከፋፍለህ ግዛ ስርዓት ሳይወናበዱ በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ እርምጃ ላይ ድምጻቸውን እንዲያሰሙና ለስርዓቱ መሳሪያ ከመሆን እንዲቆጠቡ” ጠይቋል። “የዜጎችን ጥያቄ በግድያ ማስቆም አይቻልም” በሚል ርእስ መግለጫ ያወጣው ሰማያዊ ፓርቲ፣ በአሁኑወቅት ኢትዮጵያ ነጻእንዲወጡ እገዛ ያደረገችላቸውን ጨምሮ አብዛኛዎቹ አገራት የህዝብን ጥያቄ በተገቢው የሚያዳምጡ፣ ችግሮች ሲኖሩ በጠረጴዛ ዙሪያና በሰከነ መልኩ መፍታት የሚችል መንግስት መመስረት ሲችሉ በተቃራኒው በአገራችን ስልጣን ላይ ያለው ህወሓት/ኢህአዴግን ዜጎችን በኃይል እየገዛ” እንደሚገኝ፣ በቅርቡበ አገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የተፈጸሙትን ግድያዎችና ሌሎች ህገወጥ እርምጃዎች በምሳሌነት በማንሳት ጠቅሷል። ፓርቲው” የአዲስ አበባና በዙሪያዋ የሚገኙት ከተሞች ‹‹የተቀናጀመሪፕላን ›› አስመልክቶ በስርዓቱ ላይ ጥርጣሬ የገባቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያነሱት ሰላማዊ ጥያቄ ተከትሎ በርካታ ተማሪዎችና ነዋሪዎች ህይወታቸውን ማጣታቸውን ፣ መቁሰላቸውንና መታሰራቸውን፣ ከወራት በፊት በሀረር ከተማ የተከሰተውን ቃጠሎ ተከትሎም ዜጎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ መወሰዱን፣ በባህርዳርናጎንደርከተሞች ‹‹ህገወጥግንባታነው›› ተብለው ያለካሳ፣ ቅያሬና በቂ ጊዜ ቤታቸው የፈረሰባቸው ዜጎችቤታቸው በዚህ ሁኔታ መፍረሱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጻቸው በጥይት መደብደባቸውን፣ በተለይም ጥያቄ ያነሳሉ ተብለው የተፈሩት አባወራዎች እስር ቤት ውስጥ መታጎራቸውን” አውስቷል።

“ዜጎችጥያቄያችውምንምይሁንምን ‹‹መንግስትነኝ!›› ብሎ ስልጣን ላይ የተቀመጠ አካልጥያቄያቸውን አዳምጦ በሰከነ መንገድ ምላሽ ወይንም መፍትሄ የመስጠት ግዴት የነበረበት ቢሆንም፣ ገዥውፓርቲ ግን ምላሹ ጥይት ነው” ሲል ኮንኗል።ፓርቲው በመያያዝም ገዥው ፓርቲ የዜጎችን ጥያቄ በኃይል ለማፈን የሚሞክረው ለዜጎች መሰረታዊ ጥያቄን አሟልቶ አገር የመምራት ብቃት የሌለው ከመሆኑ አንጻር ህዝብ ሌሎች በርካታ ጥያቄዎችን ያነሳብኛል ብሎ ስለሚሰጋ፣ የተነሱትንም ጥያቄዎች የመመለስ አቅም ስለሌለውና ምንም አይነት ችግር ቢኖርም ህዝብ እያስፈራራ ለመግዛት ካለው አባዜ የሚነሳ መሆኑን ጠቅሷል። አገራችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ወደ በፖሊስ መንግስትነት መለወጡዋን የሚጠቅሰው ሰማያዊ ፓርቲ፣ ኢትዮጵያ ዜጎች ሰላማዊ ጥያቄያቸውን ለመንግስት የማያቀርቡባት፣ ጥያቄያቸውን ሲያቀርቡ ምህይወታቸውን የሚያጡባት አገር እንደሆች የሰሞኑ አረመኔያዊ እርምጃ ማሳያ መሆኑን ገልጿል። ገዥው ፓርቲ በኢትዮጵያውያን ላይየወሰደውን እርምጃ ህጋዊ ለማስመሰል የባንክ ዘረፋንና ህገወጥ የቤት ግንባታን የመሳሰሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ የተወሰደውን እርምጃ ህጋዊ ለማድረግ መሞከሩም ተጠያቂነት የጎደለውና ከምክንያት የራቀ በመሆኑ፤ እነዚህ ዜጎች ላይ የተወሰደውን እርምጃ ላይ ለህዝብ በቂ መረጃ እንዲሰጥና ተጠያቂነቱን እንዲወስድም አሳስቧል፡፡ ዜጎች ህወሓት/ኢህአዴግ በፈጠረው የከፋፍለህ ግዛ ስርዓት ሳይ ወናበዱ በዜጎቻችን ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ እርምጃ ላይ ድምጻቸውን እንዲያሰሙና ለስርዓቱ መሳሪያ ከመሆን እንዲቆጠቡ እንዲሁም አገር በቀልና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቋማት፣ የሚዲያተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሚዲያዎች ገዥው ፓርቲ በህዝብ ላይ እየወሰደው ያለውን የኃይል እርምጃ እንዲያጋልጡና እንዲቃወሙ፣ እያጋለጡና እየተቃወሙ ያሉትም አጠናክረው እንዲቀጥሉ ሰማያዊ ፓርቲ ጥሪውን አቅርቧል ፡፡